# አቶ ፋና ተስፋይ

(አረጋዊ ተኽለ ማሪያም)

## ፲፱፻፵፰ - ፪ሺ፪
## (1956 – 2010)

ከ፲፱፻፹፭ ዓ.ም (1993) ጀምሮ በጄነቫ (ስዊዘርላንድ) በስደት ይኖሩ የነበሩት አቶ ፋና ተስፋዬ (አረጋዊ ተኽለማርያም) ባደረባቸው የልብ ሕመም ለረጅም ጊዜ በሕክምና ሲረዱ ከቆዩ በኋላ በመጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም (March 25 2010) በተወለዱ 54 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

በትግራይ አውራጃ በአጋሜ፣ ልዩ ስሙ ጉሎማሐዳ በተባለ ቦታ ከእናታቸው ከወ/ሮ ለተብርሃን ምራጭና ከአባታቸው ከአቶ ተኽለማርያም ገ/ማርያም የተወለዱት አቶ ፋና ተስፋየ (አረጋዊ ተኽለማርያም) ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምሮ ኢሕአፓን በመቀላቀል የሕዝባቸውን ሙሉ መብትና የኢትዮጵያ ሀገራቸውን አንድነትና ሉዓላዊነትን ለማስከበር ብሎም በሀገሪቱ ዴሞክራሲን ዕውን ለማረግ በተካሄድው ትግል ውስጥ ሕይወታቸውን በመስጠት ጭምር የተሳተፉ ቆራጥ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። ወደስዊዘርላንድ ከመጡም በኋላ የሕዝባቸውን ብሶት ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማሰማት በተካሄዱ እንቅስቃሴዎች፣ ሰላማዊ ሰልፎች ያለማሰለስ ሲሳተፉ ቆይተዋል።



የአቶ ፋና ተስፋይ (አረጋዊ ተኽለማርያም) የቀብር ሥነ ሥርዓት ወዳጅ ዘምዶች በተገኙበት
መጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም (April 1 2010) በጄኔቫ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስትያን
ተፈጽሟል።

**ኢሕአፓ ለቤተሰባቸውና ለዘመዶቻቸው፣ ለጓዶቻቸውና ለወዳጆቻቸው ሁሉ ጽናቱን ይስጣችሁ ይላል።**